በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ከማርች 21-31 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

እንዲሁም ከኤፕሪል 1-10 እና ከኤፕሪል 11-20/2025 የሚኖረው

የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2025

አዲስ አበባ

1. እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራቅ፣ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምዕራቅ እና በምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአርባምንጭ 10.1፣ በሀዋሳ 20.2፣ በኮምቦልቻ 26.9፣ በደብረ ማርቆስ 15.8፣ 14.2፣ 20.7፣ በጎዴ 39.6፣ በጅማ 36.7፣ 15፣ 22.9፣ በመተሃራ 10.7፣ በነገሌ 42.5፣ በነቀምት 10.7፣ በሮቤ 17፣ በአቦምሳ 12፣ በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 16.4፣ በአደዋ 18.6፣ በአዲግራት 26.7፣ በአለማያ 17.4፣14፣ በአለም ከተማ 54፣ በአማን 20.2፣ 29.1፣ 13.3፣ በአምባ ማሪያም 18.4፣ 12.6፣ 11.2፣ 24.6፣ 18.4፣ በአምቦ 22.7፣ በአምደ ወርቅ 34፣ በአርጆ 24.2፣ 28.6፣ 26.4፣ በአርሲ ሮቤ 11.3፣ 17.8፣ አደሌ 54፣ በበደሌ 26.2፣ በብላቴ 18.5፣ በቦሬ 17.1፣16.4፣ በቡኢ 46፣ 15.5፣ በቡሬ 22.6፣ በጭሮ 14.3፣ 11.2፣ በደምቢ ዶሎ 12.5፣ በዲላ 14.2፣ በዶሎ መና 40.3፣ 10.5፣ በኢጃጂ 42.9፣ 18.2፣ በእነዋሬ 29.5፣ 12.3፣ በፍቼ 11.6፣ በፉኙዶ 12.9፣ 14.3፣ በጋቲራ 14.7፣ 16.2፣ በገለምሶ 24.2፣ 15.7፣ በገዋኔ 59.9፣ በወሊሶ 24.7፣ በጊደ አያና 24.1፣ በጊኒር 40፣ 42፣ 26፣ በጉንዶ መስቀል 18.2፣ በቡሌ ሆራ 44.2፣ በሀረር 16.5፣ 17.4፣ በሆሳዕና 12.5፣ 18.2፣ 23.5፣ 21.8፣ 38.5፣ በእምድብር 17.4፣ 51.4፣ 22.4፣ በጎሬ 16፣ በጃራ 41.1፣ 27.1፣ 26፣ 14.5፣ በጅግጅጋ 26፣ 16.2፣ በጅንካ 11.2፣ 26፣ 15.9፣ 12.7፣ በካቿሴ 12.4፣ በኮንሶ 14.4፣ 22.5፣ 15.5፣ 12.6፣ በቁሉምሳ 47.3፣ 12.4፣ በሊሙ ገነት 23፣ 12.7፣ በማይጨዉ 11.5፣ በማጂ 16፣ 23.2፣ 24.2፣ 12.1፣ በማሻ 20.4፣ 60.4፣ በመሀልሜዳ 16.8፣ በመኤሶ 15.6፣ በመካነ ሰላም 11.3፣ 38.2፣ በምዕራብ አባያ 13፣ 11፣ በሞጣ 36፣ በሞያሌ 28.4፣ 11.3፣ 48.4፣ በንፋስ መዉጪያ 11.1፣ 27.8፣ 19.2፣ በኑራ ኤራ 16.4፣ በሳዉላ 19፣ በሰኮሩ 20.7፣ በሻምቡ 11.7፣ በሲርንቃ 11.3፣ በቴፒ 12.7፣ 22.6፣ በተርጫ 19.5፣ 14.2፣ በጽጺቃ 12.4፣ በወገል ጤና 21.5፣ 16.6፣ በወራቤ 21.8፣ 16.2፣ 49.9፣ በወረኢሉ 19፣ በወላይታ 12.2፣ 13.9፣ በያቤሎ 57.1፣ 28.3፣ በየትኖራ 12.3፣ በላሬ 12.2፣ በደንግጎ 15፣ በዶሎ ኦዶ 15፣ በግራዋ 13፣ 10.3፣ 15፣ 29፣ በጉበይሬ 25፣ ሂርና 20፣ 29.8፣ 21.5፣ 22፣ 22.3፣ ካራሚሌ 17.5፣ እንዲሁም ኩርፋጨሌ

ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

19.9፣ 62.7፣ 14.4 ሚሜ የሚደርስ ከመካለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በ23 የሀገሪቱ አከባቢዋች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 36-62.7 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል በኩርፋ ጨሌ፣ በማሻ፣ በገዋኔ፣ በያቤሎ፣ በአደሌ፣ በአለም ከተማ እንዲሁም በእምድብር ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡



ምስል፡1 ከማርች 21-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ አማሮ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ ዞኖች ፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የከንባታ፣ የሀዲያ፣ የሃላባ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ የጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ የደቡብ እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ኖጎብ፣ ኤረር፣ ፋፈን እና የሲቲ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የጋቢ፣ ሃሪ እና የማሂ ዞኖች ላይ ከ31-135 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ አማሮ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ኮንሶ ዞኖች ፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የከንባታ፣ የሀዲያ፣ የሃላባ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ የጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ የደቡብ እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ኖጎብ፣ ኤረር፣ ፋፈን እና የሲቲ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የጋቢ፣ ሃሪ፣ ፋንቲ፣ቀልበቲ እና የማሂ ዞኖች፣ ሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የመካከለኛዉኛ የምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር

በሌላ በኩል በፉኙዶ፣ በጋምቤላ፣ በላሬ፣ በመተማ፣ በጎዴ፣ በገዋኔ፣ በመተሃራ፣ በአዋሽ አርባ፣ በአይሻ፣ በምዕራብ አባያ፣ በድሬ ደዋ፣ በብላቴ፣ በቀብሪዳሀር፣ በአርባምንጭ፣ በመኤሶ፣ በአሶሳና አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35.0-43.5 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ 4) ፡፡



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1.2 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የማርች ወር ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው የበልግ አብቃይና እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተለይም የደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተስፋፋ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን በማሻሻል በልግ አብቃይ ለሆኑት አካባቢዎች የበልግ ሰብሎችን ለመዝራት እና ቀደም ብለዉ ተዘርተው በቡቃያ ደረጃ ለሚገኙ ሰብሎች እድገት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እና ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን እንዲኖር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5) ፡፡



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

1.3 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የማርች ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ባሮ አኮቦ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም በላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በገናሌ ዳዋ፣ በኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ባሮ አኮቦ እና በጥቂት ላይኛው ምስራቃዊ አባይ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በተፋሰሶች ያለውን የውኃ ሀብት እንዲጨምር ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው። በአንጻሩ ግን አብዛኛው ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን፣ በታችኛው አዋሽ፣ አባይ እና መረብ ጋሽ ተፋሰሶች ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ሰር እንደነበሩ የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 6) ፡፡



ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2 መግቢያ

የበልግ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስደው በኤፕሪል የሚዘነበው ዝናብ ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን የደቡብ ትግራይ፣ የምስራቅ አማራና የሱማሌ አካባቢዎችን ጨምሮ ከ70-120 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ10-20 ለሚደርሱት ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ማለትም የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና ሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ለ10 ቀናት ያህል እስከ 70 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ በሲዳማ ክልል እና ደቡብ ኦሮሚያ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ከ161-260 ሚ.ሜ ለ20 ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በተጨማሪም ከበልግ ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በኤፕሪል ወር በአብዛኛዉ የደቡብና የምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ40% እስከ 50% የሚደርስ የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ። በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል የመጀመሪያው አሥር ቀናት በተሻለ መልኩ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከረና እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው፡፡

2.1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለበልግ ዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በተለይም ከሳምንቱ መጨረሻ ቀናቶች ጀምሮ ይበልጥ እየተጠናከሩና እንደሚስፋፉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል (ካርታ 7) ፡፡

2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ጨምሮ የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ የሀገሪቱ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1-29 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብም፣ በደቡብ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8) ፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን

ክልል	ዞን	የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን
አሮሚያ	ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣	ከቀላል እስከ መካከለኛ
	ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምስራቅ ወለጋ፣	መካከለኛ መጠን
ደቡብ ኢትዮጵያ	ጋሞ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌድዮ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ኮንሶ፣ አሌ፣ ባስኬቶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ፣ ምዕራብ ኦሞ	ከመካከለኛ መጠን እስከ ከባድ መጠን
ሶማሌ	ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን
	ነጎብ፣ ኤረር፣ ፋፈን፣ ሲቲ፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ጃራር እና ዶሎ ዞኖች	ቀላል መጠን
አማራ	የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የደቡብ ጎንደር	መካከለኛ መጠን
	የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የመካከለኛዉ ጎንደር ዞኖች፣	ቀላል መጠን
ትግራይ	የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን
	የምዕራብ እና የሰሜን መዕራብ	ቀላል መጠን
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	መካከለኛ መጠን

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ማዕከላዊ ኢትዮጵያ	ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን
	ጉራጌ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ	ቀላል መጠን
ጋምቤላ	አኝዋክ፣ መዠንግ እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ ከመካከለኛ መጠን
አዲስ አበባ፤ ድሬደዋ እና ሐረሪ		ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን



ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-10, የሚኖረወ የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በበልግ ወቅት በመደበኛነት ትኩረት ከሚሹ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መካከል ቀን ላይ የሚኖረው የሙቀት መጠንና ሌሊት ላይ ደግሞ የሚታየው ወበቅ አንዱ ነው። በኤፕሪል የመጀመሪያዉ አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም በጋምቤላ፣ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በቤንሻንጉል-ጉሙዝና በምዕራብ አማራ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት ከ35 እንዲሁም በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከ40 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 9)።



ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

2.4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት የዝናቡ መጠንና ሥርጭት በተሻለ መልኩ በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚዳረስበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች በወቅቱ ውስጥ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ያገኛሉ፡፡

በመጪዎቹ የኤፕሪል ሁለተኛው አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎችን ጨምሮ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ሊኖራቸው እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሰሜን፣ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፤ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምስራቅ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆና አጎራባች አካባቢዎች የተሻለ ጥንካሬ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በበልግ አብቃይ አከባቢዎች በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 10) ።



ካርታ 10 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2.5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በአፕሪል ወር ከዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት መጠናከር ጋር ተያይዞ ከተቀሩት የበልግ ወራት አንጻር በጎላ መልኩ የዝናብ መጠንና ሥርጭቱ በብዙ ሥፍራዎች ላይ የሚስፋፋበት ወር ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለጎርፍ መፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

በመጪው ወር ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እንደሚጠናከሩና ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀደሙት ሁለት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል (ካርታ 11) ።



ካርታ 11 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-30, 2025 የሚኖረዉ
የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2.6 እ.አ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኤፕሪል የመጀመሪያው አሥር ቀናት ከሳምንቱ መጨረሻ ቀናቶች ጀምሮ ዋነኛ እና ሁለተኛ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ፤ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እንዲሁም በስምጥ ሸለቆ በአብዛኛው ስፍራዎቻቸው ላይ የተሻለ እርጥበት ይኖራቸዋል። ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች እና የሚመለከታቸው አካላት ከታች በተቀመጠው የግብርና ምክረ ሀሳብ መሰረት የቅድመ ጥንቃቄ ተግባራትን ከወዲሁ አጠናክሮ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

ዞኖች	የእርጥበት ሁኔታ	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
የመኸር እርጥበት ተጠቃሚ ዞኖች				
ኢሉባቦር፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ ፣ጅማ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ጎጃም፣ የደቡብ፣ የሰሜን፣ የሰሜን፣ የምዕራብ ፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የምስራቅ፣ የመካከለኛዉ ፣ የምዕራብ እና የሰሜን መዕራብ ትግራይ ዞኖች፣ አኘዋክ፣ መዥንግ ዞኖች እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ ከመካከለ እርጥበት	• የመኸር እርሻ ስራ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን • ለእንስሳት የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል • ለቋሚ ሰብሎች እድገት	• የቆላማነት ባህሪ ባለቸው አካባቢዎች ከፍተኛ ትነት የአፈር ውስጥ እርጥበትን ሊቀንስ ይችላል • ተከታታይ የደረቅ ሰሞናት መኖር	• የመኸር እርሻን ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ማከናወን • የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውኃ እቀባ ስራ ማከናወን • የዝናብ ውሃን ማሰባሰብ እና ማከማቸት • ለዘር የሚያስፈለጉ ገብዓቶችን ከወዲሁ ማዘጋጀት
በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች				

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ደቡብ ትግራይ፣ የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜን ሸዋ ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ፣ የሲዳማ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ፣ ሐረሪ፣ ቤንች ሸኮ፣ ምዕራብ ኦሞ፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ነንብ፣ ኤረር፣ ፋፈን፣ ሲቲ እና አፍዴር ዞኖች የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ ጉራጌ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ	ከቀላል እስከ ከመካከለኛ እርጥበት	• የማሳ ዝግጅት ለማድረግ • ዘር ለመዝራት • ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት	• ለሰብሎች የውኃ ፍላጎት በቂ ያልሆነ እርጥበት • ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት መኖር • ከፍተኛ ትነት የሰብሎች እርጥበት እጥረት	• ዘር ለመዘራት ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ • የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን • የደጋፊ መስኖ የዝናብ ውሃ ማሰባሰብ • በሰብል ማሳ የውሃ መከተር ማከናወን
በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች				
ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌድዮ፣ አማሮ፣ ደራሼ፣ ቡርጂ፣ ጎፋ፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ጃራር እና ዶሎ ዞኖች ኮንሶ፣ አሌ፣ ባስኬቶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ዳዋ፣ ሊበን፣ሸበሌ፣ ቆራሂ፣ ጃራር እና ዶሎ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ እርጥበት	• የማሳ ዝግጅት ለማድረግ • ዘር ለመዝራት • ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት • የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል	• ተዳፋታማ አካባቢዎች የውኃ በማሳዎች ላይ መተኛት • የአፈር መሸርሸር • የአረም መበዛት	• የተገኘውን እርጥበት በመጠቀም በደጋማ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅትና ዘር መዝራት • ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ ዝርያዎችን ከወዲሁ ማዘጋጀት • የአፈርና የውሃ እቀባና የእርከን ስራ ማከናወን • አረምን ከስር ከስሩ ማስወገድ

2.7 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኤፕሪል ወር ከቀደሙት ሁለት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እርጥበታማ ሁኔታ (Moist condition) በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ይኖኖል፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በተለይም ከማርች ወር መግቢያ ጀምሮ በተከታታይ ቀናቶች እርጥበት እያገኙ በነበሩ ስፍራዎች ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ የበልግ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች

ስልክ+2511155383994ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

እንደሚኖር የሚጠበቀው እርጥበታማ ሁኔታ እንደ ቦረና እና ጉጂ ለመሳሰሉ የከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች ዘር ለመዝራትም ሆነ ለእንስሳት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያየ ምክንያቶች የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለጀመሩና የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የሚጠበቀው እርጥበት አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ከግንዛቤ በማስገባት በቂ ግብዓቶችን ለመጠቀም ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ከበልግ ዝናብ የመዋዠቅ ባህርይ የተነሳ በአንዳንድ እርጥበት አጠር አካባቢች ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት ሊከሰት ስለሚችል የሚገኘውን እርጥበት በማከማቸት እና እርጥበትን በማሳ ወስጥ እንዲቆይ የማደረግ ሰራዎችን ለማከናወን ዝግጅት ያስፈልጋል። በሌላ መልኩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከባድ ዝናብ እንደሚኖርና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊፈጠር ስለሚችል አርሶ አደሮች ጎርፎች መደበኛ መፋሰሻቸውን ተከትለው እንዲፈሱ የማድረግ ተግባራትንና በተለይም አንዳንድ ውሃ ገብና የአፈር ፀባያቸው በቀላሉ ውሃውን በማያሰርግባቸው አካባቢዎች ባሉ ማሳዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛትን ሊያስከትልና በማሳዎች ላይ ውሃ እንዲተኛ ሊያደርግ ስለሚችል ተገቢው ትኩረት ተደርጎ የበዛውን ውሃ በቀላሉ ለማጠንፈፍና ለማስወገድ የሚያሰችሉ ዘዴዎችን ከወዲሁ ሊተገበሩ ያስፈልጋል፡፡

2.8 እ.ኤ. አ ከኤፕሪል 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀትሉት የኤፕሪል የመጀመርያ አስር ቀናት የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ያገኛሉ። ይህ ሁኔታ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰትንም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብት ክምችትን ያሻሽላል።

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉኃ ዘርፍ ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ

የውኃ ተፋሰሶች	የሚጠበቀው የእርጥበት	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
አብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ እንዲሁም የላይኛው እና መካከለኛው አዋሽ	ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት	• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል • የከርሰ ምድር የውኃ ክምችት መሻሻል • የመጠጥ ወኃ አቅርቦት መሻሻል • የመስኖ እና የሀይል ማመንጫ ግድቦች የውኃ መጠን መሻሻል	• ቅፅበታዊ ጎርፍ • በከተሞች የትራፊክ መጨናነቅ የውኃ ወለድ በሽታዎች ስጋት መጨመር	• የፍሳሽ መውረጃዎች ማፅዳት • የዝናብ ውኃ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ማሰባሰብና ማጠራቀም • ክፍት የሆኑ የውሃ ሀብት ከብክለት መታደግ • ትንበያዎችን በቅርበት በመከታተል • የመጠጥ ውኃን አክሞ መጠቀም
የላይኛው እና መካከለኛ አባይ፣ የላይኛው እና መካከለኛ ዋቢ-ሸበሌና የላይኛው ተከዜ	ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ እርጥበት	• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት በመጠኑ መሻሻል	• ከፍተኛ ትነት • ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት • የመጠጥ ውኃ አቅርቦት በቂ አለመሆን	• የሚገኘውን የዝናበ ውኃ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል ማስተዳደር • የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም • ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ተግባራትን ማከናወን
የመካከለኛና የታችኛው አባይ፣ የኦጋዴን፣ የአይሻ እና የመረብ ጋሽ ንዑስ ተፋሰሶች	ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ		• የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት መቀነስ • የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ የውኃ ማጠራቀሚያዎች የውኃ መጠን መቀነስ	• የውኃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ • የሚገኘውን ውኃ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተዳደር • የገጸ ምድር የውኃ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም • የመጠጥ ውኃን አክሞ መጠቀም

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2.9 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚጥለው የኤፕሪል ወር በአብዛኛው የበልግ ተጠቃሚ በሆኑት የኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ እና የአፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር የውኃ መጠን እንደሚያሻሽል ይጠበቃል። በተለይም የበልግ ዋነኛ እርጥበት ተጠቃሚ የሆኑ እንደ መልካ ዋከና ያሉ ግድቦች የተሻለ እርጥበት እንዲሚያገኙ ይጠበቃል። በሌላ በኩል የሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ እንደ ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ ኦሞ ጊቤ እንዲሁም ስምጥ ሸለቆ ተፋስሶች ውስጥ የሚገኙ የከተማም ይሁን ረባዳማ የገጠር አካባቢዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትልና ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል አስፈላጊ የቅድመ ጥንቃቄ ስራ ማከናወን ያሰፈልጋል። በተጨማሪም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ከተሞች የመንገዶች በውኃ መጥለቅለቅ እና የትራፊክ መጨናነቅ ሊያሰከትል ይችላል፡፡ በመሆኑም የጎርፍ ማፋሰሻ ቦዮች በጠጣር ቆሻሻ እንዳይዘጉ ክትትል ማድረግ እና ማጽዳት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች የዝናብ ውሃ ማሰባሰብያ ዘዴዎች በመጠቀም የውኃ ሀብት አቅምን ለማሳደግ ከወዲሁ የውሃ ማሰብሰብ ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል። የተቀሩት ተፋሰሶች ማለትም መረብ ጋሽ፣ የመካከለኛው እና ታችኛው አዋሽ እንዲሁም ተከዜ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et